# የፍርድቤት ትእዛዝ ማቅጠት በዲሲ- የፍቺና የማሳደግ ጉዳዮች

ፍርድ ቤት ውስጥ ወረቀት ሲያስገቡ በጉዳዩ ላይ ተሳታፊ የሆኑ ሁሉም አካላት ቅጂ ማግኘት አለባቸው። እነዚህን ቅጂዎች ለእነርሱ ማድረስ ያለበት ፍርድ ቤት ሳይሆን እርስዎ ኖት። ይህም የሂደት አገልግሎት ተብሎ ይጠራል። የተለያዩ ዓይነት ሁኔታዎች የተለያየ ዓይነት አገልግሎት ይፈልጋሉ።

## መጥርያ እና ቅሬታ መስጠት

የፍቺ ወይ የማሳደግ ፈቃድ መጠየቅ ሲጀምሩ መጀመርያ የሚያስገቡት ወረቀት ቅሬታ ነው። ቅሬታ ሲያስገቡ መጥርያ የሚባል የፍርድ ቤት ቅፅ ያገኛሉ። አስፈላጊ የሆኑ የፍርድ ቤት አቤቱታዎችን በ www.dcbar.org/pleadings ወይም በዲሲ ከፍተኛ ፍርድቤት የቤተሰብ ፍርድ ቤት መቀበያ ማእከል (500 Indiana Avenue NW፣ ክፍል JM-540) ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8:30 a.m. እስከ 5:00 p.m. ክፍት ስለሆነ እዛ ያገኛሉ።

ይህን ክስና መጥርያ ቅጂ ለሌኛው በዚህ ክስ ውስጥ ድርሻ ላለው ወገን መስጠት ይኖርቦታል። መጥርያና ክስን ከሚከተሉት በአንዱ መንገድ ማቅረብ አለቦት፡

1. *የግል አገልግሎት፡* በጉዳዩ ላይ ድርሻ የሌለው አዋቂ ክሱንና መጥርያውን ለሌላኛው ወገን እንዲሰጥሎት ማድረግ። ይህን እራስዎ ማድረግ አይችሉም። ጓደኛ፣ ዘመድ ወይ ባለሙያ ሰጪ እንዲሰጥሎት መጠየቅ ይችላሉ። ሌላኛውን ወገን በአካል በሚያገኙበት ማንኛውም ቦታ መስጠት ይችላሉ፡ ለምሳሌ እቤት ውስጥ፣ ስራ ቦታ ወይ መንገድ ላይ።
2. *ምትክ አገልግሎት ቤት ውስጥ፡* በዚህ ጉዳይ ላይ ድርሻ የሌለውን ግን ሌላኛው ወገን በሚኖርበት ቤት ውስጥ የሚኖር አዋቂ ሰው ክስ እና ቅሬታውን እንዲሰጥልዎ መጠየቅ ይችላሉ። ይህን እራስዎ ማድረግ አይችሉም። ጓደኛ፣ ዘመድ ወይ ባለሙያ ሰጪ እንዲሰጥሎት መጠየቅ ይችላሉ።
3. *እውቅና ያለው ፖስታ፣ መመለሻ ደረሰኝ ጥያቄ፡* መጥርያውንና ክሱን እውቅና ባለው ፖስታ ለሌላኛው ወገን እንዲደርስ ማድረግና ደረሰኝ መቀበል። ፖስታ ቤት በመሄድ እርስዎ ማድረግ ይችላሉ። ደብዳቤዎ ከደረሰ በኋላ ፖስታ ቤቱ መድረሱን የሚገልፅ ደረሰኝ (አንዳንዴ ‹‹አረንጓዴ ካርድ›› ተብሎ ይጠራል) ይልክሎታል። በፖስታ ለመላክ ምርጥ የሆነ ውቦታ ለሌላኛው ወገን የቤት አድራሻ ነው። ሌላኛው ወገን ወይም በሌላኛው ወገን ቤት የሚኖረው አዋቂ ሰው ይህን አረንጓዴ ካርድ መፈረም ይኖርባቸዋል።

## መጥርያውንና ክሱን በምን ያህል ግዜ ውስጥ መስጠት አለብኝ?

60 ቀናት አሎት። ተጨማሪ ግዜ ከፈለጉ፣ ለቤተሰብ ፍርድ ቤት የመቀበያ ማእከል ሁለተኛ መጥርያ እንዲሰጦት መጠየቅ የሚችሉ ሲሆን ይህም ሌላ 60 ቀናት ይሰጥዎታል። የመጀመርያው መጥርያ ቀነ ገደብ ሳያልፍ ሁለተኛ መጥርያ መጠየቅ ይኖርቦታል። ከዚህ በኋላ ተጨማሪ ግዜ ከፈለጉ፣ ጥያቄዎን ለዳኛ ማቅረብ አለቦት።

## ክስና መጥርያውን መስጠቴ በምን አረጋግጣለሁ?

ሌላኛው ወገን ከሰጡ በኋላ በቤተሰብ ፍርድ ቤት ማእከል መቀበያ ማእከል እንደሰጡ ቃሎን መስጠት ይኖርቦታል። ይህ ሌላኛው ወገን በምን መልኩና መቼ መጥርያው እንደተሰጣቸው

የሚገልፅ መሀላ ያለው መግለጫ ነው። ይህን ካላስገቡ በስተቀር ፍርድ ቤቱ ጉዳዮን አይቀጥልም።

ወረቀቱን የሰጠበት መንገድ መሰረት በማድረግ ቃሉን ለማስገባት የተለያዩ መንገዶች አሉ።

1. *የግል አገልግሎት፡* ወረቀቱን የሚሰጠው አዋቂ ሰው ቃላቸውን መፃፍ ይኖርባቸዋል።
2. *ምትክ አገልግሎት ቤት ውስጥ፡* ወረቀቱን የሚሰጠው አዋቂ ሰው ቃላቸውን መፃፍ ይኖርባቸዋል።
3. *እውቅና ያለው ፖስታ፣ መመለሻ ደረሰኝ ጥያቄ፡* ቃለመሀላውን አጠናቀው የተፈረመውን አረንጓዴ ካርድ ማያያዝ አለብዎ።

በሚያስፈልገው የጊዜ ክልል ውስጥ ክሱንና መጥሪያውን ካልሰጡና በተጠቀሰው ግዜ ላይ ቃሉን ካስገቡ ጉዳዮ ተቀባይነት ስለሚያጣ ሂደቱን እንዳዲስ መጀመር ይኖርቦታል።

### ሌላኛውን አካል ማግኘት ካልቻልኩስ?

በማሳተም ወይ በመለጠፍ መንገድ ለመስጠት ማስገባት ይችላሉ። መጀመርያ ሌላኛውን ወገን ለማግኘት ጥረቶችን ማድረግ ይኖርቦታል። ያደረጉትን ጥረትም መግለጫው ላይ ማካተት ይኖርቦታል። ዳኛው መግለጫው ላይ ስለወሰኑት ውሳኔያቸው ፍርድ ቤት ችሎት ወይም በፖስታ ያሳውቆታል። ዳኛው በቂ የሆነ ጥረት እንዳላደረጉ ከወሰኑ የሚያደርትን ጥረት መቀጠል እና የጠፋውን ሰው ማግኘት ካልቻሉ ሌላ መግለጫ ማስገባት ይችላሉ።

1. *በማሳተም ማሳወቅ፡* ማሳተም ማለት ማስታወቅያ በጋዜጣ ላይ መለጠፍ። ዳኛው መግለጫውን ከፈቀዱ፣ ማስታወቅያውን ለማሳተም ወደ ቤተሰብ ፍርድ ቤት ማእከላዊ መቀበያ መሄድ አለቦት። ማስታወቅያው በሁለት ጋዜጣዎች ላይ በሳምንት አንድ ጊዜ ለሶስት ሳምንት መውጣት አለበት።
2. *በመለጠፍ ማሳወቅ፡* መለጠፍ ማለት በፍርድ ቤት ውስጥ ማስታወቅያ መለጠፍ ማለት ነው። ማስታወቅያ ለማሳተም አቅምዎ ካልቻለ፤ ከመታተም ይልቅ ማስታወቅያው እንዲለጠፍ መጠየቅ ይችላሉ። ክፍያ እንዳይከፍሉ ከተፈቀደሎት ይህንን በመግለጫዎ ላይ መግለፅ አለቦት። ካልሆነ ስለ ፋይናንስ ሁኔታዎ በመግለጫዎ ላይ መረጃዎትን ማካተት የሚያስፈልግዎ ሲሆን ዳኛው ማስታወቅያ ከሚታተም መለጠፍ የሚፈቀድ መሆኑን ይወስናል። የመለጠፍ መግለጫው ከተፈቀደ የፍርድ ቤት ፀሀፊው ለሚያስፈልገው 21 ቀናት ማመልከቻውን የሚለጥፍ ይሆናል።

### በማሳተም ወይ በመለጠፍ መስጠቴን በምን አረጋግጣለሁ?

1. *በማሳተም ማሳወቅ፡* ጋዜጣው የመታተሙ ማረጋገጫ ለፍርድ ቤት ይልካል።
2. *በመለጠፍ ማሳወቅ፡* የፍርድ ቤት ፅህፈት ቤቱ ሁሉንም ነገር ስለሚያጠናቅቅ የፅሁፍ ማረጋገጫ መስጠት አይጠበቅቦትም።

## ከመጀመርያ ክስ በኋላ የፍርድ ቤት ወረቀት መስጠት

በአጠቃላይ፣ ምላሽ ወይ ሞሽን የመሳሰሉ ማንኛውም በጉዳይ ላይ ያሉትን ወረቀቶች ቅጂ በጉዳዩ ላይ ተሳታፊ ለሆኑ አካላት መሰጠት አለበት። አብዛኛው ግዜ እነ ዚህ ወረቀቶች በመደበኛ አንደኛ ደረጃ ፖስታ መላክ ይችላሉ። ሌላኛው ወገን ጠበቃ ካላቸው ወደ ጠበቃው ይላኩት።

ሌላኛው ወገን ጠበቃ ከሌላቸው በቀጥታ ወደ ባለጉዳዩ በፖስታ ይላኩት። በተጨማሪም ወረቀቱን በአካል ለጠበቃ ወይ ሌላ አካል መስጠት ይችላሉ።

**ከመጀመርያው ክስ በኋላ፣ ለሌላ ፍርድ ቤት ትእዛዝ መስጠቴን በምን መልኩ አሳያለሁ።**

መጀመርያ ካስገቡት ክስ ውጪየ ፍርድ ቤት ወረቀት ሲያስገቡ፣ መጥርያ የሰጡት ማንነት፣ እንዴት (በፖስታ ወይ በእጅ መስጠት)፣ በየትኛው አድራሻና የሰጡበትን ቀን መመዝገብ አለቦት።

## የመጨረሻ ትእዛዝ ከወጣበኋላ የፍርድ ቤት ወረቀት መስጠት

በአጠቃላይ፣ ጉዳዮ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ወይ ትእዛዝ ከተሰጠ ከ60 ቀናት በኋላ ሞሽን ወይ ሌላ ክስ ካስገቡ ወረቀቱ ክስ ወይ መጥርያ ባስገቡበት መንገድ ይሰጣል።